TPES PTA TIMES
Takoma Park Elementary School
Jump into learning!

7511 Holly Avenue
Takoma Park MD 20912
Phone: 301-650-6414
http://montgomeryschoolsmd.org/schools/takomaparkes/
http://www.tpespta.org/
Join the PTA listserv:
Send an email to TPES-subscribe@yahoogroups.com

September 2008

**IMPORTANT Date Changes for Mixers!!!**
The **Kindergarten Mixer** will be on Tuesday, September 9, at 6:45 pm, and the **First Grade Mixer** will be on Monday, September 15, at 6:45 pm. The **Second Grade Mixer** remains on its previously scheduled date, Thursday, September 18, at 6:45 pm.

## የሁለት ደቂቃ ማብራሪያ ከፒቲኤ መሪዎች
## ሽሙኤል ሾሃምና ኒና ጋርፊልድ

በፒቲኤ አስተዳዳሪዎች ስም ለመጪው የትምህርት አመት እንኳን ደህና መጣችሁ እንላለን። በዚህ አመት  የተኮማ ፓርክ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪዎች ትብብራችንን ባለማቃረጥ መልካም አመት እንደሚሆን ብንተማመንም መጪውን አመት ትምህርት ቤታችን ወደ ግሮስቨነር የሚዘዋወርበትን እቅድ ማውጣቱ ከበድ ሊያደርገው ይችላል።

የፒቲኤው አስተዳዳሪ ኮሚቴ ፒቲኤው የሚያዘጋጃቸውን ፕሮግራሞችና የተለያዩ በአሎችን ለመጪው አመት ያለምንም ችግር እንዲከናወን ባለፈው በጋ ሲሰሩ ከርመዋል። ዝግጅቶቹም ከትምህርት ባሃላ ያሉትን ፕሮግራሞች እንደ የአለም አቀፍ ምሽት የፊልም ምሽት የኪንደር ጋርደን አንደኛና ሁተኛ ክፍል የሚገናኙበት ምሽት እንዲሁም  የንባብ እርዳታ የሚሰጥበትንና የመሳሰሉትን ይሆናል። እነዚህም ፕሮግራሞች ለተማሪዎች የተለያዩ ልምዶችን በማበርከት ለትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎትና ለአስተማሪዎች እርዳታን በመስጠት እንዲሁም ጠንካራ የወላጆች ማህበር በመመስረት ለትምህርት ቤቱ ብልፅግና ይሰጣሉ። እነዚህንም የፒቲኤውን አላማዎች ማሟላት ከቻልን ምንም አይነት መሰናክል ማሸነፍ አይሳነንም።

አመቱንም የጀመርነው የኮሚቴውን አባሎችና ረዳቶችን በመለየት የዝግጅቶች ቀናት በመመደብ ባጀት በማውጣትና አዲሱን የተኮማ ፓርክ ፒቲኤ ዌብሳይት በማዘጋጀት (ዌብ ሳይቱን በማዘጋጀት ለተባበረን ሰካት ዋርድን ሳናመሰግነው አነልፍም) ነው። በዚህም ዌብሳይት ላይ የዝግጅቶችንና የአመት በአል ካላንደር ማንኛውንም እርዳታ ማበልፀግ የምትችሉበትን መንገድ ስለፒቲኤ ስብሰባና ህጎች  መዋጮን በተሞረኮዘ ደሞ ስለ ሳሌ ፎስተር የሴፍ ዌይና ጃይንት የረድኤት ፎርም ሌላም አርንገብጋቢ ጉዳዮችንን የመሳሰሉትን ማየት ትችላላችሁ።

ፒቲኤውም ቅድሚያ የሚሰጠው የትምህርት ቤቱን ወደ ግሮስ ቨነር መዛወር ፕላን ማውጣት ለወላጆች ትምህርትን በተመለከተ ያሉትን ሁኔታዎች ማሳወቅና የተለያዩ ማህበረሰቦችን ለማሰባሰብ የአማርኛና የስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪ ተወካዮች የፒቲኤው ቦርድ ውስጥ ማሳተፍ ይሆናል።

የመጪውም መልካም አመት እንዲሆንልን የወላጆችን ተሳትፎ እንቀበላለን። አትክልት በመኮትኮትና በማስተካከል ተማሪዎችን ትምህርት በማስጠናት በክፍል ውስጥ መርዳት ለተለያዩ ዝግጅቶች ምግብ በማዘጋጀት የግሮስ ቨነር ሽግግር ፕላን ላይ በመሳተፍ የቋንቋ ማስተርጎም እርዳታ በመስጠት ወይም የተለያዩ የፒቲኤ ዝግጅቶች ላይ በመሳተፍ መተባበር ትችላላችሁ።

በዚህ አመት ለመተባበር በፈቃደኝነት የተመዘገባችሁ ወላጆች ትልቅ ምስጋና እናቀርባለን። ሶስት አመት በቶሎ ስለሚያልፍ ተሳትፎዋችሁን ማበልፀግ የምትሹ ወላጆች እርዳታችሁን ለመስጠት አትዘግዩ።

---

## የልጃችሁን ክፍል ወላጆች አስተባባሪ ሁኑ

የፒቲኤው በዚህ አመት ምኞቱ በእያንዳንዱ ክፍል አንድ አስተባባሪ ወላጅ እንዲኖር ነው። የወላጁም ሃላፊነትከአከልጆት አስተማሪ ጋር በመማከር አስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች በማሟላት ነው። ከነዚህም ዋነኛው ሌሎች ወላጆች በክፍል ውስጥ ለአስተማሪው እርዳታ የሚሰጡበትን ቀናቶች ማቀናኘትና መዝግቦ ለአስተማሪው ማቅረብ ይሆናል። ከበታች የተከተሉትም ዝርዝሮች ከእያንዳንዱ ክፍል አስተማሪዎች በህብረት የተወጣጡ ናቸው።

ኪንደር ጋርደን
- የንባብ መፃህፍቶችን ማስተካከል
- የቤት ስራ ኮፒ አድርጎ ማከፋፈል
- በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በሚቀያየሩበት ግዜ እርዳታን መስጠት
- ስእሎችን ወይም ፅሁፎችን መለበድ

አንደኛ ክፍል

- ወላጆች በክፍል ውስጥ የሚዘጋጁ የተለያዩ ድርጊቶች ላይ እንዲሳተፉ ማስተባበር
- በክፍል ውስጥ ለሚዘጋጁ ድርጊቶች የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማስተካከል
- ወረቀቶች ኮፒ ማድረግ
- የንባብ መፃህፍቶችን በማስተካከል ፋይል ማድረግ

ሁለተኛ ክፍል

- በወር ወላጆች የሚሳተፉበትን ሊስት ለአስተማሪ ማዘጋጀት
- በዲሰምበር የሚከናወነው የሙዚቃ ጨዋታ የወላጆችን እርዳታ ማስተባበር ( ለምሳሌ ልብስ መስራት)
- በሜይ ወር የሚደረገው ፔኒ(አንድ ሳንቲም) የሚሰበሰብበት ግዜ ፔኒዎችን ወደ ባንክ ወስዶ አስቆጥሮ ለክፍሎቹ ስጦታ ማበጃጀት።
- በአመቱ መጨረሻ ላይ በሚደረገው ፒክኒክ ላይ መተባበር

የክፍል ወላጆት አስተባባሪ በተጨማሪም ወላጆች እርስ በእርስ በመነጋገር ለአሸተማሪ ስጦታ ለመስጠት እንዲያመች የወላጆችን ስምና ቁጥር በማከፋፈል ሊተባበሩ ይችላሉ። ይህን ለማድረግ የምትሹ ከሆነ ፍራንሲስ ኩክጋ በስልክ ቁጥር 301-588-3044 በመደወል ወይ ደሞ በኢሜል cookf@gao.gov ማሳወቅ ይችላሉ።

---

በተኮማ ፓርክ ትምህርት ቤት ኤክፖለርስ ክለብ ፕሮግራም ላይ ይሳተፉ!

ይህ ለልጆቻችን በጣም ጠቃሚና ትምህርታዊ የሆነ ፕሮግራም የኮሚቴ አባል በመሆን የሚሳተፍ ፈቃደኛ ወላጅ ያስፈልጋል። በዚህም ፕሮግራም ተማሪዎች  ሙዚየሞች የእርሻ ቦታዎችና ሌላም የተለያዩ ቦታዎችን የማየት እድል ያገኛሉ። በቅድሚያ ለተወሰኑ ተማሪዎችና ረዳት አስተማሪዎች ቦታ ከተሰጠ በኋላ ለተቀረው የትምህርት ቤት ህብረሰብ አነስተኛ ገንዘብ በማስከፈል ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ ይችላሉ። ልጆቻቸውን ይዘው ለሚመጡ ወላጆች መግቢያው ነፃ ይሆናል። የኮሚቴው አባል ለመሆን የምትሹ ሱዜት ማክፈርሰንን ደውለው በማነጋገር ወይ ደሞ ኢሜል ማድረግ ትችላላችሁ።
በስልክ ቁጥር 301-920-0829
suzettemcmurray@yahoo.com.

## Volunteer Spotlight

አኒ ፓወር (ከበታች ያለ ፎቶ ይመልከቱ) ቅዳሜ ኦገስት 23 የተለያዩ ወላጆችን በማሰባሰብ አትክልቶችን በማስተካከልና አረሞችን በማረም ውሃ አጠጥተዋል። እነሱም ኤለና ማርኮ ራሲ፣ አንጀላና ዳኒየላ ግሪንፊልድ፣ ሩት ፖልክ አሮንና ኢተን ሾሃም፣ ኒናና ቤላ ጋርፊልድ፣ ስቲቭና ሩቢ ሹማከር እንዲሁም ካሮል ፓወር ነበሩ።



---

ፒቲኤ የርሶን እርዳታ ከበታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ይፈልጋል!

- የኮሚቴው አባል ረዳት መሪ በመሆን።
- የጁላይ አራት ሰልፍ ኮሚቴ በመሆን።
- የልጆች ክብደት መጨመር ያሳስቦታል? የእርምጃና የሩጫ ክለብ።

---

## PTA Executive Committee

**Co-Presidents (contact at info@tpespta.org)**
- Nina Garfield
- Shmuel Shoham

**Co-Vice President**
- Julie Farb Blain

**Treasurer**
- Pam Loprest

**Co-Secretaries**
- Frances Cook
- Cathy Ocheltree

Additonal contact information may be found on the PTA web site at http://www.tpespta.org